የኩፍኝ በሽታ (ሩቤላ)

የኩፍኝ በሽታ ምንድን ነው?

ኩፍኝ (የጀርመን ኩፍኝ)ሩበላ ተብሎ የሚጠራው ኩፍኝ፣ በቫይረስ የሚመጣ ከፍተኛ ተላላፊ በሽታ ነው። የኩፍኝ ቫይረስ በቀላሉ የሚሰራጭ ሲሆን በአንድ ሰው ጤና ላይ ከባድ የሆኑ ተጨማሪ በሽታዎችን ሊያስከትል ይችላል። ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉ የክትባት ጥረቶች ኩፍኝ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እንዳይስፋፋ አድርገዋል ነገር ግን ወረርሺኞች አሁንም ሊከሰቱ ይችላሉ እንዲሁም አሁን እየተከሰቱ ነው። በማህበረሰቦች ውስጥ ያለው የክትባት መጠን ዝቅተኛ በሚሆንበት ወይም በሚቀንስበት ጊዜ በሽታው የመሰራጨት እድሉ ይጨምራል። ኩፍኝ በብዙ የአለም ክፍሎች የተለመደ ሲሆን ባልተከተቡ መንገደኞች ምክንያት ወደ አሜሪካ ሊገባ ይችላል። ከፍተኛ የክትባት ሽፋን መጠበቅ ሰዎችን እና ማህበረሰቦችን ከወረርሺኙ ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው።

የኩፍኝ በሽታ ምልክቶች ምንድ ናቸው?

- ሽፍታ እና
- ትኩሳት እና
- ሳል ወይም በፈሳሽ የተሞላን አፍንጫ ወይም የደብዘዝ ያሉ አይኖች

አንድ ሰው ለኩፍኝ በሽታ ከተጋለጠ በኋላ ከስምንት እስከ 12 ቀናት ውስጥ የበሽታ ምልክቶች ይታያሉ። አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያው ምልክት ትኩሳት ነው።አብዛኛውን ጊዜ ሽፍታው ትኩሳቱ ከጀመረ ከሁለት እስከ ሶስት ቀናት በኋላ የሚታይ ሲሆን ከአምስት እስከ ስድስት ቀናት ይቆያል። ሽፍታው ከጸጉር ስር ጀምሮ፣ ወደ ፊት እና ወደ ላይኛው አንገት ይሄዳል ከዚያም ወደሰውነት ይወርዳል።

እርስዎ ወይም ልጅዎ የኩፍኝ በሽታ ምልክቶች ካለባችሁ ምን ሊያደርጉ ይገባል?

ከሐኪምዎ ወይም ከክሊኒክዎ ጋር እስከሚነጋገሩ ድረስ ቤት ውስጥ ይቆዩ እንድሁም ጎብኝዎችን ከመቀበል ይቆጠቡ። ለጉብኝት መምጣት ካለብዎት ሃኪምዎ ወይም ክሊኒክዎ ይነግርዎታል።

የኩፍኝ በሽታ ምን ያህል ከባድ ነው?

ኩፍኝ ሆስፒታል ተኝቶ መታከም አልፎ ተርፎም ሞት ሊያስከትል የሚችል ከባድ በሽታ ነው። የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ብዙ ሰዎች እንደ ተቅማጥ፣ የጆሮ ኢንፌክሽኖች፣ የሳንባ ምች ወይም ሃይለኛ የአንጎል ብግነት (ዘላቂ የአእምሮ ጉዳት የሚያስከትል የአዕምሮ ኢንፌክሽን ችግር ይኖራቸዋል)። ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት እና ዕድሜያቸው ከ 20 አመት በላይ በሆኑ አዋቂዎች ላይ ህመሞች ይበልጥ የተለመዱ ናቸው።

በእርግዝና ወቅት የሚመጣ የኩፍኝ በሽታ ያለጊዜው ለሚመጣ ምጥ፣ ለጽንስ መጨንገፍ እና ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ሕጻናት ለመውለድ የመጋለጥ አደጋን ይጨምራል። በተለይ የኩፍኝ በሽታ የሰውነት የበሽታ ተከላካይ ስርዓታቸው ደካማ በሆኑ ሰዎች ላይ ከባድ ሊሆን ይችላል።

የኩፍኝ በሽታ እንዴት ይዛመታል?

የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ሲተነፍሱ እና ሲያስሉ በአየር አማካኝነት ይዛመታል። በጣም ተላላፊ ነው። የኩፍኝ በሽታ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊይዝዎት አይችልም፣ ምክያቱም ከያዝዎት በኋላ፣ በሽታውን የመከላከል አቅም ይኖርዎታል።

የኩፍኝ በሽታ ያለበት ሰው ለምን ያህል ጊዜ አስተላላፊ ይሆናል?

ኩፍኝ ያለበት ሰው ሽፍታው ከመታየቱ በፊት ከአራት ቀናት ሽፍታው ከታየ በኋላ እስከ አራት ቀናት ድረስ ወደሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፍ ይችላል።

ለኩፍኝ በሽታ ህክምና አለው?

አይ፣ ለኩፍኝ በሽታ ምንም የተለየ ህክምና የለም። የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች አልጋ ላይ እረፍት ማድረግ፣ ፈሳሾች እና ትኩሳትን መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። እንዲሁም እንደ ተቅማጥ፣ የጆሮ ኢንፌክሽን ወይም የሳንባ ምች ላሉ ህመሞች ህክምና ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

ለኩፍኝ በሽታ ክትባት አለ?

አዎ። አብዛኛውን ጊዜ የኩፍኝ ክትባቱ ከጆሮ ደግፍ በሽታእና ከጀርመን ኩፍኝ (MMR) ጋር ይተዋሃደ ነው።

- ልጆች ዕድሜያቸው ከ12-15 ወራት ሲሆን እና ከ 4-6 አመት ሲሆናቸው የ MMR ዶዞችን ያገኛሉ፤ ሁለተኛው MMR ከመጀመሪያው ዶዝ አንድ ወር በኋላ ወዲያውኑ ሊሰጥ ይችላል።
- አለም አቀፍ ጉዞ ለሚያደርጉ ወይም ወረርሽኙ በሚከሰትባቸው ቦታዎች ለሚሄዱ ዕድሜያቸው ከ 6-12 ወር ለሆኑ ህጻናት የ MMR የመጀመሪያ ዶዝ ይመከራል።
- ኩፍኝ ይዟቸው የማያውቅ ወይም የኩፍኝ ክትባት ያልወሰዱ አዋቂዎች በተለይም 1957 ወይም ከዚያ በኋላ የተወለዱ ከሆኑ አንድ ዶዝ የ MMR ክትባት ሊወስዱ ይገባል።
- ተማሪዎች (የኮሌጅ ተማሪዎችን ጨምሮ)፣ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች እና አለም አቀፍ ተጓዦች ሁለት ዶዝ የ MMR ክትባት መውሰድ አለባቸው፣ ካልተከተቡ፣ ሊከተቡ ይገባል።
- እርስዎ ወይም ልጅዎ ምን አይነት ክትባቶች እንደሚያስፈልጋችሁ ጥያቄዎች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

እርስዎ ወይም ልጅዎ ለኩፍኝ በሽታ ከተጋለጡ ምን ሊያደርጉ ይገባል?

- ወዲያውኑ ለሃኪምዎ ወይም ለክሊኒክዎ ይደውሉ። ለጉብኝት መምጣት ካለብዎት የሚያሳውቁዎት ይሆናል።
- ካልተከተቡ በተጋለጡ በሶስት ቀናት ውስጥ የ MMR ክትባት መውሰድ በኩፍኝ በሽታ ከመያዝ ሊከላከል ይችላል።
- ለኩፍኝ በሽታ ከተጋለጡ በስድስት ቀናት ውስጥ የኢሚውኖ ግሎቢን (ለኩፍኝ ቫይረስ ጸረ እንግዳ አካላት የያዘ የደም ምርት) ከወሰዱ የኩፍኝ በሽታን ሊከላከል ወይም ክብደቱን ሊቀንስ ይችላል።

በትምህርት ቤት ወይም በሌላ ቦታ (ለምሳሌ፡- የበጋ ዘመቻ፣ የህጻናት እንክብካቤ፣ የስራ ቦታ፣ ክሊኒክ) የኩፍኝ በሽታ ከተገኘስ?

MDH እና የአካባቢ የጤና መምሪያዎች የተጋለጡ ሰዎችን ለመለየት፣ ለኩፍኝ በሽታ ያላቸውን በሽታ የመከላከል አቅም ለመገምገም እና ለዚያ ልዩ ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ የድህረ ተጋላጭነት ፕሮፊላክሲስ ለመምከር ከአካባቢው ጋር የሚሰሩ ይሆናል።

Minnesota Department of Health
PO Box 64975, St. Paul, MN 55164-0975
651-201-5414 | www.health.state.mn.us/measles

04/24/2025 (Amharic)

ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት በሚከተለው ላይ ይደውሉ፡- 651-201-5414።.